# ዕዘኑ ለቀሪ

የመቅደላው ውል ቋጠሮ
የተቀበረው በማሰሮ
የሚስጢሩ ገመና
ለስልጣን ለንግስና
ለመግዛት ተደላድሎ
ከጠላት ጋር ወግኖ
መይሳውን አስገድሎ
በወረሰው ሀይል መቅኖ
በትረ_መንግስቱን ካሳ
የጨበጠበት ጠባሳ
ደረስጌን በውቤ ብሎ
የቂም ብድሩንም ከፍሎ
ፋይሉ ተዘጋ ያለን ዋሾ
የጎንደሮች መሬት ቁርሾ
ገና ያስደረድራል ሙሾ።
ያችን የሙታን ዕናት
አጉል ድከሚ ብሏት
ያለ ፋይዳ ከንቱ ልፊ
ዘርሽንም በዘር አጥፊ
ለማለት ይመስላል መልዕክቱ
ለታዘበው ሰው ኩነቱ።
ለባለ ቀኑ ድሎት
የማይጓደል አቅርቦት
ይረጋገጥ ዘንድ ታልሞ
የራሱን ኩራዝ አጨልሞ
በየመብራቱ ምሰሶ ስር
ዘብ መቆሙ ደብረታቦር
ምፀቱ ለገብርየ ለገልሞ
ነገሩ በግራሞት አስደምሞ
የትንቢቱ ቅላጼ መዋዕሉ
ለካስ ጊዜ ኖሯል ባለድሉ።
ጊዜ በይኖ ለሁሉም
ላንደኛው ሲያበራ
ለሌኛው እንዲጨልም
በጎንደሮች መከራ

ዙሪያ ገባዋን አጥራ
ኩራት ለሚሰማት ለባለጊዜዋ
ለዕልቂት አዝማሪዋ
ሞቷን በቂም ቋጥራ
መቃብሯን ቆፍራ
ሳታውቀው አቅራሪ
ልጧ ለተራሰው ዕዘኑ ለቀሪ
ወራሿ ለሆነው በዕዳዋ ተጧሪ።
ጥር 1998
abraham beyenne